# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 22

ሰኔ 12 ቀን 2014 ዓም(19-06-2022)

ይህ ሳምንታዊው አገር እንዴት ሰነበተች ትንቅራችን የሚያተኩረው በያዝነው ሳምንት ባዬናቸውና በሰማናቸው አብይት ጉዳዮች ላይ ሲሆን በምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ የገባችው አገራችን ብዙ ክስተቶችን አስተናግዳለች፤ከነዚያም ዋናዋናዎቹም  በጋዜጠኞችና የማህበረሰብ አንቂዎች፣በመንግሥት ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ግለሰቦች ላይ የሚደርሰው መንገላታት፣በአማራው ማህበረሰብ በተለይም በፋኖ ላይ የሚካሄደው ዘመቻ ያደረሰው ጉዳትና ውጤቱ፣በአገራችን ውስጥ የሰፈነው የኑሮ ውድነት፣ ሰላም ማጣትና ጦርነት፣በፓርላማ አባላቱ የቀረበበትን ጥያቄ መሪው አብይ አህመድ የሰጠው መልስና የአገራችን የወደፊቱ እጣ ፈንታ ምን እንደሚመስል የሚተነትን ይሆናል።

በመጀመሪያው ነጥብ ወደ ጋዜጠኞቹና የማህበረሰብ አንቂዎችና ተቃዋሚዎች ስናተኩር የሚከተለውን ይመስላል።

በነዚህ ዜጎች ላይ የተጀመረው ማሳደድ፣አፈናና ግድያ አሁንም በስፋት እንደቀጠለ ነው። በዬቀኑ የሚታሰር በመኖሩ፣ነገ የማን ተራ እንደሚሆን ስጋትና ጭንቀቱ እንደጨመረ የሚያሳይ እንጂ የትናንትናው እስረኛ ሲፈታና ማሳደድ ሲቆም ፣በዘላቂነት ፍትህ ሲከበር አልታዬም።አንዱ ሲፈታ ሌላው ይታፈናል።የሥርዓቱ ቁንጮ አብይ አህመድም በግልጽ የሚቃወመው ሁሉ ይቀፈደዳል ሲል መረን የለቀቀ ዛቻ ማሰማቱ የዚሁ ሂደት ማለቂያ ቢስነቱን የሚያረጋግጥ ነው። ፍርድ ቤት ለይስሙላ በገንዘብ ዋስትና የለቀቃቸውን ተከሳሾች የፖሊሱ ተቋም መፈጸም ሲገባው አሻፈረኝ በማለት ከፍርድ ቤት በላይ በመሆን አዲስ ክስ እዬመሰረተ ንጹሃኑ በአስከፊ የእስር ቤት ኑሮ እንዲማቅቁ ማድረጉን ቀጥሎበታል።ከብዙ አንዱን የክስ መሠረት ብናነሳ ከዚህ በፊት በምምህር መስከረም አበራ ላይ የቀረበው የኬንያ ሽልንግ ተገኝቶባታል የሚለው ክስ መሳቂያ የመሆኑን ነገር ሳንረሳ  በዛሬው የሳምንቱ መግቢያ ላይ ሌላ ተጨማሪ ካለፈው የበለጠ ከት አድርጎ የሚያስቅ፣ከሳሹን የሚያጋልጥ  በቤቷ ውስጥ 65 መጽሃፍና ብዙ የታተሙ ወረቀቶች አግኝተንባታል የሚል ክስ ፖሊስና አቃቤ ሕጉ ይዘው መነሳታቸው የስርዓቱን  ይሉኝታ ቢስነትና መበስበስ ያዬንበትን አጋጣሚ ፈጥሯል። መምህር መስከረም ሙያዋ  በምርምርና ጥናት ውስጥ እንድትገባ የሚያስገድዳት በመሆኑ ብዙ መጽሃፍትን የማንበብ፣ የማጥናትና የመመርመር ብሎም የመተቸት መብቷ የተጠበቀ ነው።ተማሪዎች የነጠረ እውቀት ባለቤት እንዲሆኑ የሚያበቃቸው  ዋናው መሣሪያ መምህራኑ  የብዙ መጽሓፍት አንባቢ ሲሆኑ ነው።መስከረም አበራንም መምህር የሚያሰኛት የዚያ ችሎታ ባለቤት መሆኗ ነው።ያንን ያላደረገ መምህር መምህር አይባልም። ወጣቱን የዕውቀት ባለቤት ለማድረግና፣ከዘመኑ ጋር አብሮ እንዲሄድ፣ከቀረው ዓለም ወጣት እኩል እንዲሰለፍ፣ለአገርና ለተከታዩ ትውልድ ውል ያለው ነገር ሰርቶ ለማስረከብ እንዲበቃ መምህራኑ የተለያዩ መጽሃፍቶችንና ጥናቶችን መመልከታቸው ግዴታና አስፈላጊ ነው።

መጽሃፍ ማንበብና መያዝ ወንጀል ነው ከተባለ የዬትምህርት ቤቶቹ መጽሃፍት ቤቶች፣የምርምር ተቋማትና ብሔራዊ ቤተመጽሃፍትም የወንጀል መደብሮችና  በውስጣቸውም ያሉ ሠራተኞችና ተጠቃሚዎች በሙሉ ወንጀለኞች ናቸው ማለት ነው።የዕውቀት ጸር ካልሆኑ በቀር ማንበብና መመራመር መጽሃፍ መሰብሰብና መጻፍ ወንጀል የሚሆንበት ምንም አይነት ሕጋዊ መሠረት የለም። ወንጀለኛንና ወንጀልን የሚያበዛው ከእውቀትና ከማንበብ የራቀ፣በድንቁርና ዓለም ውስጥ የሚኖር ማህይም፣እንደሰው የማያስብ ያውሬ መንፈስ የሚነዳው ህብረተሰብና ግለሰብ ብቻ ነው።በዚህ መንፈስ

የሚነዳ ፖሊስና የሕግ ተቋም ነገ ደግሞ መጽሓፍ ቅዱስና ቁርአን አገኘንበት/አገኘንባት ብለው ሰውን ከማሠር የሚመለሱ አይሆኑም።ምክንያቱም ሁለቱም መጽሓፍት ናቸውና!

በንጉሱ ጊዜ ማንበብ ወንጀል የሆነው ንጉሡንና ሥርዓቱን የሚነቅፍ መጽሃፍና ጽሑፍ መያዙ ነበር። የመንግሥት ማተሚያ ቤት በሆነው በብርሃንና ሰላምና በሌሎቹም ታትመው የሚወጡ ሥርዓቱን በግልጽም ባይሆን በተዘዋዋሪ የሚነቅፉ ፣የሌሎችን አገሮች እድገትና የዴሞክራሲ አሠራር ከአገራችን ጋር እያመዛዘኑ የሚተቹ ጽሑፎች ነበሩ።ከነዚያም ውስጥ አንዱና የታወቀው፣ከሕዝቡ እጅ እንዳይገባ የሚከለከለው በአቶ አቤ ጉበኛ የተጻፈው "አልወለድም" የሚለው አነስተኛ መጽሓፍ ነበር።በአምባገነኑ የደርግ ዘመንም የሚተቸውንና የሚቃወመውን ጽሑፍና መጽሓፍ ከአንባቢውና ከጸሃፊው ጋር ለማጥፋት ብዙ ግድያዎችና እስራቶችን ፈጽሟል።የነዚህ ሁሉ ጥረት ግን ሕዝቡ ይበልጥ በጉጉት እንዲያነባቸው አደረገው እንጂ እንዳሰቡት አልሆነላቸውም።የሰው ልጅ በተፈጥሮው እልኸኛ ነው፤ አታድርግ ያሉትን ለማድረግ፣የማያውቀውን ለማወቅ የሕሊና ግፊትና ጉጉት ያድርበታል።ይህ ከአዳም ጀምሮ ይዞት የመጣው የመፈታተን ፍላጎትና ጸባዩ ነው።ጉጉቱም የሚዘረጋበትን ግንብና አጥር እንዲጥስ ያደርገዋል።የራበው ሰው ይሉኝታና ፍርሃት አያውቅም፣ያገኘውን ለመብላት ይቋምጣል፤ይስገበገባል፤ አትብላ ቢሉት እሺ አይልም።እውነትና እውቀትን የሚሻ ትውልድም እንዲሁ ነው።ለመማርና ለማወቅ ይጥራል፤ያነባል፣ይጽፋል።ትውልድንና አገርን ቅጠል በመበጠስና በጥንቆላ መገንባት አይቻልም።

መጽሃፍና ጸሓፊዎች የተፈጥሮን ምስጢር የሚቃኙና የሚያጋልጡ፣ዓለማችንን እንድናውቅ የሚረዱን መነጽሮቻችን ናቸው፤መከበርና በእንክብካቤ ልንይዛቸው ይገባል።በእነሱ ላይ የሚደርስ ጥቃት በአገርና በሕዝብ ላይ የሚደርስ ጥቃት ነው።መንግሥትም ቢሆን ቢያውቅበትና ቢታደል የጸሓፊዎቹን ሃሳብና አስተያዬት እንደ ትልቅ አጋዥ ሊቆጥር በተገባ ነበር።ስህተቱን ሲነግሩት ለመታረም የሚፈልግ በአክብሮት ይንከባከባቸዋል እንጂ ጠላት አድርጎ አያሳድዳቸውም።ጠቡ ከእውቀትና ከእውነት ጋር የሆነ ሲሆን ግን በመጀመሪያ የጥቃት ሰለባ የሚሆኑት ጸሃፊዎችና ተችዎች ይሆናሉ።የጥሩ ሃሳብ ጸሓፊዎች ብቻም ሳይሆኑ መጥፎ ሃሳብ ናቸው የምንላቸውንም ቢሆን የሚጽፉትን ማክበር ይገባል። ሃሳባቸውን ባንቀበለውም ለመሞገት የምንችለው የጻፉትን ስናነብ ነው።ብዕር የሚገል መሣሪያ ሳይሆን ድክመትና፣ድንቁርናን የሚያሸንፉበት ሰላማዊ መሳሪያ ነው።

በጠላትነት ተፈርጀው በእስር ቤት የሚማቅቁት የሰማንያ ዓመት አዛውንት የሆኑትም አቶ ታዲዮስ ታንቱና ብዙዎቹ የተወነጀሉበት ምክንያት የታሪክና የሃቅ ባለቤቶች በመሆናቸው፣በማንበብና በመጻፍ የዳበረ እውቀታቸውን ለሌላው በማካፈላቸው ነው።እውቀት ወንጀል በሆነበት አገርና ማህበረሰብ ውስጥ እንደነዚህ አይነቶቹ ኩራዝ የሆኑ ሰዎች በነጻነት የመኖርና የመንቀሳቀስ፣ሃሳባቸውን የመግለጽ መብታቸው አይታወቅም።እንደወንጀለኛ ይቆጠራሉ።እነዚህ ሰዎች ታፍነው የት እንደገቡ ሳይታወቅ ወጥተው መቅረታቸውን ስናከልበት ያገራችንን የሕግ አሰራር ከፍትሕ መስመር ምን ያህል እንደራቀና በተቃርኖ ውስጥ እንደቆመ ፣ለእውቀት ባዳና ጠላት የሆነ ሥርዓት መስፈኑን ማሳያ ነው።ትግላቸው ለፍትሕ መስፈን ስለሆነ ፍትሕ እንዲሰፍን ሌላውም መታገል ይኖርበታል።ታዲዮስም ሆኑ ሌሎቹ ለራሳቸው ብቻ ፍትሕ ይከበርልኝ አላሉም።የቆሙትና የሚከራከሩት፣መከራና ስቃይ፣በአገራችን ያሰፈነው ጎሰኛ አገር አጥፊ ፖለቲካና ፖለቲከኞች እንዲወገዱ፣ ለማህበራዊ ፍትሕ፣ለሰብአዊ መብት፣ ለአገራዊ አንድነትና ክብር፣ሁሉም በእኩልነት ለሚታይበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፈን ነው።ምንም እንኳን እንደነሱ በእስር ቤት ውስጥ ባይታጎርም በሕሊናው የታሰረና በፍርሃት ድባብ ውስጥ የሚኖር ሁሉ እስረኛ ነው።ያ ደግሞ ከፖሊስ እስርቤት ይበልጣል።ስለሆነም ከማይታዬው ግን ከተተበተበበት ሰንሰለት ለመውጣት የነሱን አርማ ተከትሎ በትግሉ ተሳትፎ ለውጥ ማምጣት አለበት።ያ ካልሆነ ከላይ እንደገለጽነው በተራ ወደ መታረጃው ቄራ እንደሚነዳ ከብት መሆን ነው፤ ተቃዋሚውን

በማሰቃዬትና በማስፈራራት በመግደልና በማሳደድ በሥልጣኔ ላይ እኖራለሁ ብሎ የሚያስብ ቢኖር ከታሪክ የማይማር፣ በራሱ የድንቁርና ዓለም ውስጥ የሚኳትን፣የገዛ መቃብሩን የሚቆፍር አብሪተኛ ብቻ ነው።

ተቃዋሚን እያታለልኩና እዬደለልኩ እኖራለሁ የሚልም ለጊዜው ይሆናል እንጂ የማታ ማታ ማንነቱ ሲታወቅ ማጠፊያ ያጥረዋል።አብይ አህመድም ገና ከጅምሩ የነገረን የሚፈልጉትን ሳር እዬሰጠሃቸው ወደ ቄራ ንዳቸው፣ከዚያም በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን ብለህ ተርትባቸው የሚል ነበር፣ተረቱን በተግባር እዬተሮጎመው አሳይቶናል።እያሳዬንም ነው።ከእኛም መካከል ከበሬው የባሱ እጃቸውን በእጃቸው እዬቆረጡ ለሁሉም የሚታገሉትን በማሳደዱና በመግደሉ ላይ የተባበሩ አልጠፉም፤ እዬተባበሩም ነው።ይዋል ይደር እንጂ ወደ ቀልባቸው ለመመለስ ካልቻሉ ከሚያገለግሉት ስርዓት ጋር አብረው የመወገድ ዕድላቸው ትልቅ ነው።አንዳንዶቹም ፈራ ተባ እያሉ በመዋዠቅ ላይ ናቸው።የሰፌድ ላይ ውሃ ሆነዋል።ሌሎቹም በፍርሃትና በጭንቀት የነበሩበትን ቦታ እዬለቀቁ እግሬ አውጭን በማለት ላይ ናቸው።የአልሞት ባይ ተጋዳይ፣ የእውር ድንብር እርምጃም በመውሰድ ላይ ያሉ አልጠፉም። ውጤቱ ግን የሚዝናኑበት አልሆነም።ተግባራቸው ይበልጥ ከሕዝብ እዬነጠላቸው እንጂ እያቀራረባቸው አልመጣም።

አማራ ሳይሆን ከአማራው በላይ ለአማራው የሚከራከረውና በታሪክ ማስረጃ የኢትዮጵያ ጠላት የሆኑትን ሰንጎ የያዘው አቶ ታዲዎስ ታንቱ በእስር ቤት መሰንበቱ ሳያንሰው ባደረበት ጉዳት ለበሽታ ተጋልጦ በመሰቃዬት ላይ ይገኛል።ለይስሙላ ለሕክምና ቢወሰድም በዕድሜ፣በሕመምና በድካም የዛለ እጁን በሰንሰለት አስሮ ወደ ሃኪም መወሰዱን ስንመለከት ሥርዓቱ ምን አይነት አረመኔ መሆኑን ብናውቅም ለማያውቀው ያረጋግጥለታል።በውጭና በአገር ውስጥ ያለው አገር ወዳድ ታዲዮስ ታንቱና ሌሎቹም ጋዜጠኞችና የተቃውሞ ድምጽ የሚያሰሙ ዜጎች ከእስር እንዲፈቱ መጮህ ይኖርበታል። ለአገር ህልውና ከሚደረገው ትግል ተለይቶ አይታይም።

የሕዝቡ ተቃውሞና ትግል ሲያይል የመንግሥት ነኝ ባዩ ጎራ ብርክ ውስጥ በመግባት እርስ በርሱ እዬተባላ የሚያደርገው ጠፍቶታል።የሕዝቡን ጥያቄ በመመለስና ባለመመለስ ንትርክ ውስጥ ገብቷል። ይህንን የሚያሳዬን አፍኖ በቁጥጥር ስር አውሏቸው ከነበሩት መካከል የጀነራል ተፈራ ማሞ፣ የአማራ ክልል የልዩ ሃይል ፖሊስ ኮሚሽነር ይሰጥ ጌታሁን፣የጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይ፣የጋዜጠኛ ታምራት ነገራና ከሁለት ቀናት በፊት መምህር መስከረም አበራ በገንዘብ ዋስትና መለቃቃቸው ነው።ሆኖም ግን የተለቀቁት በዋስ እንጂ ከክሱ ነጻ በመሆን ስላልሆነ ዳግም ላለመታሰራቸው ዋስትና የለም።

የመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን የሆነው ሙሃመድ እንድሪስ በሰጠው መግለጭ አንድም ጋዜጠኛ በቁጥጥር ስር የዋለ የለም ሲል ሽምጥጥ አድርጎ ከዷል።እንደ ሰውዬው አገላለጥ የተያዙት በሙያው ያልሰለጠኑና እውቅና የሌላቸው ጋዜጠኞች ሳይሆኑ የፖለቲካ ዓላማ ይዘው ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሚንቀሳቀሱ ወንጀለኞች ናቸው ብሏል።ከተያዙት ውስጥ ምንም እንኳን ስሙን ባይጠራም ተመስገን ደሳለኝን የጋዜጠኝነት እውቅና ይዞ ለእኩይ ዓላማ የተሰለፈና የብሔር ቅራኔን በመፍጠር የተሳሳቱ መረጃዎችን የሚያቀርብ ስለሆነ በሕግ መጠዬቁ ተገቢ ነው ብሏል።በሥርዓቱ በጋዜጠኝነት ለመታወቅ የቻሉት ጋዜጠኛም ባይሆኑ ወይም የጋዜጠኝነትን ስነምግባር የማያሟሉ ለሥርዓቱ የሚያገለግሉ አድርባዮች ብቻ ናቸው።እንዲህ አይነቶቹ ሲሸለሙና ሲወደሱ እንጂ ሲኮነኑ ታይቶ አይታወቅም።የማታ ማታ ግን አወዳደቃቸው አያምርም። አሁንም ሕዝብ ፍርዱን እዬሰጣቸው ይገኛል፤ኩስ የነካው እንጨት አድርጓቸዋል፤ የሚረጩትን የቅጥረኛ ፕሮፓጋንዳ ላለመስማት ከወሰነ ውሎ አድሯል።

አገራችንን እንደፈለኩት አድርጌ በሥልጣን ላይ እኖራለሁ የሚለው የኦሮሙማው ቡድን የጥፋት ጉዞውን ቀጥሎበታል።እመሰርታታለሁ ብሎ ለሚያስባት የመናብ አገር ኦሮሚያ በኤኮኖሚ ግንባታ ስም ከባቢውን ከሌላው በሚቀማው ባጀት እዬገነባ ነው።ነገ በእጄ ትገባለች ብሎ የሚያስባትን አዲስ አበባ የፖለቲካ ማእከልነቷን ነጥቆ የገባያ አዳራሽ ለማድረግ አቅዶ ደፋ ቀና ይላል።በኢትዮጵያ ስም ከዓለም አቀፍ ተቋማትና አገራት የሚገኘውን ብድርና እርዳታ ከሚዘርፈው የተረፈውን ለከንቱ ውዳሴ በልዩ ልዩ ፕሮጀክት ላይ እያፈሰሰው ይገኛል።በግንባታና በእድሳት ስም የዘረፈውና ያወጣው ብዙ ቢሊዮን ብር ሳይበቃው አሁን ደግሞ በከተማዋ ለዘመናት ተገንብተው የኖሩ የመንግሥት ተቋማት፣ ሚኒስትሪዎችና ቢሮዎችን ወደ ገጠራማ ቦታ አዛውራለሁ በሚል እብደት ከ60 ቢሊዮን ብር በላይ መመደቡን ይፋ አድርጓል።ባለፈው ሰሞን ቤተመንግሥት በ49.9 ቢሊዮን ብር እገነባለሁ ብሎ ካለውና የከተማዋን ሕንጻ በሙሉ በግራጫ ቀለም እቀባለሁ ብሎ ከመደበው የ30 ቢሊዮን ብር ጋር ይህ ተጨማሪ ወጭ ለምን እንዳስፈለገው የሚያውቀው እራሱ መንግሥት ነኝ ባዩ ቡድን ቢሆንም ለሕዝቡ ስውር አይደለም።ችግሩ የመስሪያ ቤቶቹ ህንጻ ቀለሙና በአዲስ አበባ ውስጥ መሆኑ ሳይሆን የሰፈነው ጎሰኛ ሥርዓት በተከላቸው ተቋማት ህንጻዎች ውስጥ የሚርመሰመሰው የመንግሥት አካልና ተጠሪ፣ በኢትዮጵያዊነት ሥራውን ባግባቡ ለመፈጸም አለመቻሉ ነው። ግንቡ በሌላ ቦታ ቢሠራ በውስጡ የሚካሄደው እኩይ ሥራና ሠራተኞች ካልተለወጡ መሻሻል አይኖርም።የፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት 15 ፎቅ ሕንጻ በመስራቱ የፖሊሱን አሰራር አላሻሻለውም፣የፍርድ ቤቱም፣የደህንነቱም፣ሌላውም እንዲሁ። አሁንም የተለያዩ የሚንስትር መሥሪያ ቤቶች ወደሌላ ቦታ ቢዛወሩና በአዲስ መንደር ውስጥ ቢጠቀጠቁ ሥርዓቱ ይለወጣል ማለት አይደለም።በአንጻሩም በባህላችን ያገር ሽማግሌ ሲያካሂድ የኖረው የፍርድ አሠራር በዛፍ ሥር ተቀምጦ በመሆኑ ፍርድን አላዛነፈውም። ፍትሕን ፍትሕ የሚያሰኘው የችሎት ቤቱ ማማርና መተለቅ ሳይሆን ለፍትሕ የቆሙ ሰዎችና ተቋም መኖሩ ነው።

ሰሞኑን በፍትህ ሚኒስትሩ በጌዴዎን ጢሞቲዎስ የሚመራ ቡድን በአውሮፓ የሥራ ጉብኝት ለማድረግ በወጣበት እግረመንገዱን ቤልጅዬም ከተማ ብራስልስ በሚገኘው ኤምባሲ አዘጋጅነት ኢትዮጵያውያንን በአካልና በበይነመረብ(በዙም)ለድጋፍ ጥዬቃ ስብሰባ አካሂዶ ነበር።ተሰብሳቢዎቹ ያነሱት የፍትሕ ጥያቄ መኖር አለመኖሩን የሚገልጽ ማብራሪያ ባይወጣም ከአብይ አህመድ የተለዬ መልስ ይሰጣል ተብሎ አይጠበቅም።አንዳንዶቹም ሳንጠይቅ ከመሥመሩ አሶጡን፣ዘጉብን ብለው ምሬታቸውን የገለጹ አልጠፉም።ይህ የሚያሳዬው ደጋፊዎች ብቻ እንዲሳተፉ ፣ሌላው ተቃዋሚ ነው የሚባለው እንዳይሳተፍ የማድረግ እርምጃ መሆኑ የሚያሳዬው በፍትሕ ዙሪያ የሚስተናገድ ጥያቄ አለመኖሩን ነው።

ኦሕዴድ የሚያደርገው ሁሉ ኦሮሚያ የተባለ አገር እመሠርታለሁ ባለው ዕቅዱ መሠረት መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፣ብዙሃኑ ግን የነቃ አይመስልም።በአብይ አህመድ የማጭበርበሪያ ቃላት የደነዘዘ ይመስላል።አዲስ አበባን ትርጉምና ዋጋ ቢስ እናደርጋታለን ያሉትን ይህ የምኒስትሮች መሥሪያ ቤት ነቀላ አንዱ ማሳያ ነው። በከተማዋ የተለያዩ የኦሮሚያ ተቋማትን ሲተክሉ የነበሩና ኢትዮጵያዊነትን የሚያንጸባርቁ ተቋማትንና ታሪካዊ የቅርስ ይዞታዎችን ያፈራርሳሉ። ኢትዮጵያንም ከዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ እይታና መድረክ ላይ ለማሶገድና በሂደት የኦሮሚያን ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልብ ኤምባሲ ለመትከል በቅርቡ ከሰላሳ በላይ በውጭ አገር ለብዙ ዓመታት የኖሩ ኤምባሲዎችን ወጭ ለመቀነስ በሚል ሰበብ የመዝጋቱ እርምጃ የዚሁ ደባ አካል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የእብሪተኛው የኦሕዴድ አነግ መሪ የሆነው ሽመልስ አብዲሳ እንደ አንድ ልዑላዊ አገር መሪ በጅቡቲ ውስጥ በተካሄደ የቀጠናው ስብሰባ ላይ መሳተፉ ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኗል። ለስሙም ቢሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባለበት አገር የዚህ የአንድ ክልል መሪ በዚህ ደረጃ መገኘቱ የኦሮሙማው አገር የመሆኑን ሂደት ከምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ነው።ነገ ደግሞ በአፍሪካ ሕብረትና በተባበሩት

መንግሥታት ስብሰባ ላይ ላለመገኘቱ ዋስትና የለም።በኤኮኖሚ፣በፖለቲካ ዘርፍ የሚያካሂዱት ዘመቻ ሕዝብን በማፈናቀልና ሌላውን ከባቢ ከመውረሩ ጋር ተደምሮ ሲታይ የኦሮሚያ አገራዊ ግንባታ ከማይካድ ደረጃ ላይ መድረሱን ያረጋግጥልናል።

ወያኔም በበኩሉ ትግራይ የሚባል አገር ለመመስረት ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ይመስላል።ችግር የሆነበት በጠባቡና በደረቁ የትግራይ መሬት ሕዝቡን ለማስተዳደር አለመቻሉ ነው።ለዚያም ነው የራያና አዘቦን፣የወልቃይትና ጠገዴን ለም መሬት ካላገኘሁ እሞታለሁ ብሎ በጉልበትም በአጋሮቹም ድጋፍ ለማግኘት የሚሯሯጠው።ሁለቱ አገር አጥፊ ሃይሎች የጋራ ጠላት ያደረጉት የአማራውን ማህበረሰብ ከላይ፣ከጎንና ከኋላው ከበው ለማዳከም ጥረት እያደረጉ ያሉት ለዚሁ የጋራ ህልማቸው ነው።

የክልል መሪዎች በዬከባቢ አጎራባች ወደብ ባለቤት በሆኑ አገሮች የሚደርጉትን እሩጫ ያዬንበት ሳምንት ነበር።አብይ አህመድ በሞቃዲሾ፣ሙስጠፌ በበርበራ፣ሽመልስ አብዲሳም በጅቡቲ መሄዳቸው ነገ አገር ቢሆኑ የወደብ ችግር እንዳይገጥማቸው በቅድሚያ ትስስራቸውን ለማጥበቅ እንደሆነ መገመት ይገባል።ወያኔም ኤርትራን በጉልበት እይዛለሁ ብሎ የሚፍጨረጨረው ቢችል ኤርትራን ጠቅልሎ አለያም ቁርሶ ወደብ ያላትን ነጻ ትግራይ እመሥርታለሁ ብሎ ነው።ጠርጥር ገንፎም አለው ስንጥር ነውና!ትልቋ ኢትዮጵያ የራሷ ወደቦች በነበሩና፣በራሷ ልጆችና በውጭ ሃይሎች ደባ ባጣቻቸው ደቃቃ ሃገር ተብዬወች እግር ሥር ወድቃ ስትንከባለል ከማዬት የበለጠ ለአገር ወዳጁ ኢትዮጵያዊ አንጀት የሚልጥ በሽታ የለም።

ወደ ፓርላማው ውሎ ስናመራ ብዙ አሳዛኝና አሳፋሪ ክንውኖችን ለማዬት ችለናል።

አንድ የአገር መሪ በፓርላማ መደበኛ ስብሰባ ላይ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ማብራሪያና መልስ የመስጠት ግዴታ አለበት።ይህ ግዴታ ግን በኢትዮጵያ መሪዎችና የፓርላማ አባላት የሚታወቅ ሆኖ አልታዬም።አብይ አህመድ በ13ኛው የፓርላማ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘቱ እንደ ግል ውሳኔውና በጎፈቃድ፣ ከመሪ የማይጠበቅ ደግነትና ቅንነት ተደርጎ በፈረደበት የፓርላማ አዳራሽ የተሰበሰቡት ውታፍ ነቃዮች ከሚያቀርቡት ፍሬ ከርስኪ ጥያቄ በላይ ምስጋናቸውን ሲያስተጋቡለት ታዝበናል።አጨብጫቢና አስጨብጫቢ በሚገኝበት በዚህ አይነቱ ፓርላማ ውስጥ የተሰበሰቡበት በተፈለገበት አቅጣጫ የሚነዱ እንስሳት የታጎሩበት በረት እንጂ መንግሥትን ወጥሮ የሚይዝ የሕዝብ ተወካዮች የሚሰበሰቡበት ፓርላማ ሆኖ አልታዬም።ጥቂቶቹ የሕዝቡን ጥያቄና ወቅታዊ ችግር ያነሱ ቢሆንም አብዛኛው ትኩረት የሰጠው የመጣበትን አካባቢ የኤኮኖሚ ጥቅምና ድርሻ የሚመለከት ነበር።ምናልባትም ለነዋሪው አስቦ ሳይሆን ከሚገኘው ተቋዳሽ ለመሆን ካላቸው ፍላጎት ሊሆን ይችላል።የጥቅም ሽርክና ከፓርላማ ወለል ላይ መገለጹ በታላላቅና ሃብታም አገሮችም የሚታይና የማይካድ አሠራር ነው።ፓርላማ ሎቢይስት የሚቅበዘበዝበት የጨረታ መድረክ ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም።በዚህ ስብሰባ ላይ ከታደሙት ውስጥ አንዳንዶቹም መንግሥት ማድረግ የሚገባውን ለዚያውም በቁንጽል ደረጃ ያደረገውን እንደ ትልቅ ግብአት የመንግሥትን ብቻ ሳይሆን የአብይ የድካም ውጤትና ደግነት ቆጥረው ለማጨብጨብና ለማስጨብጨብ የቃጣቸውንም ታዝበናል።የራያ ሰፊ መሬት በወያኔ ተይዞ ሕዝቡ ተፈናቅሎ፣ ያልተፈናቀለው የመረረ ኑሮ ሲገፋ ከዚሁ አካባቢ መጣሁ ያለችው የፓርላማ አባሊት በፈረቃ ለሚዳረሰው አነስተኛ የኤሌክትሪክ አቅርቦት አብይ አህመድን ለማመስገን የሄደችበት መንገድ የአድርባይነትን ጥግ ፍንትው አድርጎ ያሳዬ ነው።የሌሎቹም እንዲሁ።

በዚሁ ፓርላማ ላይ በተለይም በአብን አባላት በክርስቲያን ታደለና በዶር ደሳለኝ ጫኔ የተነሱት አማራውን የሚመለከት ጥያቄ በአብይ ላይ ያሳደረው ብስጭትና ንዴት በግልጽ ሲታይ የተሰጠው

መልስና ማብራሪያ የማናናቅና የማቅለል ብሎም የመንግሥትን እኩይ ተግባራት የሚያወድስና ለማጠናከርም የታሰበ ነበር። ጠያቂዎቹ ያላነሱትን በመከላከያ ውስጥ ያለውን የጎሳ ስብጥር አብይ ሆን ብሎ ሌሎቹ የተነኩና የተወቀሱ አድርጎ በማቅረብ የአማራውን የሙብት ጥያቄ ፣በመከላከያያውና በልዩ ሃይሉ ሰላምና ሕግ በማስከበር ስም የሚፈጸመው ግፍና በደል እራሱ ሕግ ያላከበረ ነው የሚለውን ነቀፋ አብይ አህመድ ዘሎ መከላከያ ውስጥ ያለው ኦሮሞና ደቡብ እንዲሁም ሌላው ክልል ተወላጅ በሁመራና በራያ የአገሩን ዳርድንበርና ሰላም ለማስከበር ሲዋደቅ  መቃወምና ወራሪ ማለት ከጠላት እንጂ ከወገን የማይጠበቅ ተግባር ነው በማለት የከፋፋይና የጥላቻ መልእክቱን አስተላልፏል።ከዛም አልፎ ወንበዴና ሽፍታ  በልዩ ልዩ ስም ሕዝብ ሲዘርፍና ሲገል መንግሥት ዝም ብሎ አያይም፤ ሕግ ያስከብራል ከማለት አልፎም መከላከያ ብቻ የታጠቀውን ጥቁር ክላሽ ሌላው ገሎ ካልወሰደ በቀር ሊያገኘው አይችልም በማለት የፋኖን ስም ባይጠራም ከመከላከያ አባላት እየቀማና እዬገደለ የታጠቀ ዘራፊና  ሌባ ነው ሲል በግልጽ ሰድቦታል። ሕግ የማስከበሩን እርምጃ ሕዝቡ ሰላማችንን መለሰልን ብሎ የደገፈው ሲሆን ዘላቂ ሰላም እስኪሰፍን ድረስ ዘመቻው ይቀጥላል ብሏል።በተግባር የሚታዬው ግን ዘመቻው እንዳልተሳካና የሕዝቡም ተቃውሞ እዬጠነከረ መሄዱን ነው።ይህንኑ ጥቁር ክላሽ የኦነግ አሸባሪ በኦሕዴድ ፈቃድ መታጠቁን ሳይገልጸው ሸውዶ ቢያልፈውም አደባባይ የወጣ ምስጢር ነው።

ኢትዮጵያ ፈርሳለች ወይም እናፈርሳታለን የሚሉት  ከንቱ ምኞት ነው፤ አትፈርስም።ምንም እንኳን ችግር ቢበዛም እንደሌሎቹ አገራት እንደ ጃፓን፣ጀርመንና ኮሪያ ችግሯን አልፋ በትልቅነት ትኖራለች በማለት የተለመዱ ማማለያ ቃላቶቹን ደርድሯል።አብይ አህመድ ለማምታታት ያቀረበው የያገራቱ ታሪክ የሚያሳዬው ግን የጠቀሳቸው አገራት እንደ ኢትዮጵያ በጎሳና በጸረ አንድነት ሃይሎች መዳፍ ሥር የወደቁና የሚታመሱ አገሮች አለመሆናቸው ነው።በጠቀሳቸው አገሮች የጎሳ ማንነትና ንትርክ ቦታ አልነበረውም፤ ሁሉም በአንድ ቋንቋ የሚናገር፣ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የተሰለፈ፣  በአንድ አገራዊ መንፈስ የቆመ ሕዝብ ታግሎ ከጥፋት ያዳናቸው አገራት ናቸው።

በዚሁ በፓርላማው ውሎ ጊዜውን ያጠፋው በእሱ አመራር ላለፉት ጥቂት ዓመታት እንዴት የልማት ግንባታና የኤኮኖሚ እድገት በእጥፍ ደረጃ እንዳደገ በመግለጽ ላይ ነበር። የኑሮ ውድነቱን የተጠቃሚው ብዛት ያመጣው  ነው ሲል የቀድሞ መሪውን የመንፈስ አባቱን የመለስን ቀልድ ደግሞታል።መለስ ሱካር ለምን ጠፋ ሲባል ዱሮ ሱካር ቀምሶ የማያውቀው ገጠሬ ስለሚጠቀም ነው ብሎ ነበር ፣አብይም በጠላ ሳይቀር በሁሉም የምግብ ዝግጅት ሱካር መጠቀም ስለተለመደ ነው በማለት በሕዝቡ ችግር ተሳልቋል።የሌላውን አቅርቦትም ማነስና ከገባያው መጥፋት  ምናልባት ሕዝቡ ልዩ ልዩ ምግብ መመገብ ስለለመደ ነው ሳይል ይቀራል አንልም።በሥራ አንታማም፣የሚያሙን የማይሠሩት ናቸው ሲል የተሠራውን የመንገድ እርዝማኔ፣የውጭ አገር ምንዛሬ ገቢ እድገት፣የውጭ ገበያ ልውውጥ በእጥፍ ማደግ፣በአዲስ አበባ  ትምህርት ቤቶች በነጻ የምግብ አቅርቦት--- የመሳሰሉትን እንደ ማስረጃ አቅርቧል።ሲጀመር በልቶ ማደር የሚችል ሕዝብ ለልመና እጁን አይዘረጋም።ምንም እንኳን ደሃ ልጆች እንዳይራቡ ምግብ ማብላቱ የሚነቀፍ ባይሆንም ለዚያ የዳረጋቸው ሥርዓቱ የፈጠረው ድህነት ስለሆነ ሥርዓቱን ቅዱስ አያደርገውም።ለምኖ መብላት ቅስም ይሰብራል፣ሞራል ይነካል።ልጆቹ በቤታቸው ቆሎም ሆነ ቂጣ በልተው ቢያድጉ ከልመና የተሟላ ገበታ የበለጠ ደስተኞች ይሆናሉ። ሌላው የተመጻደቀበት ጉዳይ በግንባታ መስክ ያቀረበው ዝርዝር ነው።

እንኳን የአንድ ልዑላዊ አገር መንግሥት ነኝ ባይ ቀርቶ የንግድ ተቋምም ቢሆን የግንባታ ሥራዎችን ማካሄድ ግዴታው ነው።ሌላው  ቀርቶ የውጭ ወራሪ ቢሆንም እንኳ ለራሱ ጥቅምና አገልግሎት ሲል አንዳንድ የግንባታ ሥራዎች ያካሂዳል።መንገድ ይቀይሳል፣የስልክ አገልግሎት ይዘረጋል---ወዘተ ጣልያን እስከአሁን ድረስ መተኪያና አማራጭ የሌለውን የደብረሲና ጣምራ በርን ተራራ በስቶ አዲስ አበባን

ያገናኘው፣በተለያዩ ከተማዎች ሕንጻ የሠራው ፣በደቡብ አፍሪካም በዘረኞቹ ሥር በነበረችበት የሙቶ ዓመት ዕድሜ ብዙ ተቋማት ተገንብተዋል።የተቋማት መገንባት የሥርዓትን ፍትሓዊነት አያሳይም። በወያኔም ጊዜ የተገነቡ መኖራቸው አይካድም። በኦሕዴድ ጊዜም እንዲሁ። በሁለቱም ቡድኖች የሥልጣን ዕድሜ ሕዝቡ የበይ ተመልካች ሆነ እንጂ የትሩፋቱ ተካፋይ አልሆነም።ተቋማቱን ፍትሓዊ የሚያደርገው ሕዝባዊ ሥርዓት ሲሰፍንና ተቋማቱን ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ ሲያደርግ ነው። በኦሮሚያ ባሉ ተቋማት ኦሮሞ ያልሆነው ማህበረሰብ እኩል መጠቀም ካልቻለ፣በነጻ መንቀሳቀስ ሳይችል በየመንገዱ የሚታረድ ከሆነ የመንገዱ መዘርጋትም ሆነ የተቋማት መኖር ሊያኮራው አይችልም፤ሥርዓቱንም ፍትሓዊ አያደርገውም።

ከሁሉም በላይ ለፓርላማ አባላቱና ለሕዝቡ ያለውን ንቀት በቁሻሻነት ሲገልጸው ጫማውን ማጽዳት፣ ጥርሱን መፋቅ ያለመደና የማይወድ ስለንጹህ ቤትና አገር ሊያስብ አይችልም።ንጹህ ኑሮና አዲስ ነገር ሲሠራ የሚቃወሙት በቁሻሻ ኑሮ የሚረኩ ብቻ ናቸው በማለት ለግንባታው ቅደም ተከተል ይኑረው፣ ገንዘቡ በሆነ ባልሆነው አይባክን፣በቅድሚያ የሕዝቡ መደበኛ ኑሮ ይሟላ፣ይሻሻል፣መብቱ ይከበር፣ የአገር አንድነትና ልዑላዊነት ይረጋገጥ፣የጎሳ ፖለቲካና ክልል የተባለ የልዩነት አጥር ይፍረስ---ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያነሱትን ለመምታት የመዘዘው የቃላት ዱላ ብልግናውንና እብሪቱን ያሳዩበት ነበር።አያይዞም የሚሠራ ሰው አያባክንም፣ገንዘቡን እንዴት እንዳመጣው ስለሚያውቅ አወጣጡንም ያውቅበታል ሲል እራሱን በራሱ ጠልፎ ጥሎታል።ታዲያ በብድርና በእርዳታ የሚገኝ ገንዘብ ላላስፈላጊ ፓርክና ቤተመንግሥት ፣ለሚንስትር መሥሪያ ቤቶች መንደር ግንባታ ገንዘብ ማውጣቱ ከምን አንጻር ሊታይ ይችላል?የሚል ጥያቄ ለማንሳት እንገደዳለን።

የፓርላማውን ውሎ ከመቋጨታችን በፊት ከወያኔ ጋር ድርድር መካሄዱን ተጠይቆ በሰጠው መልስ ምንም አይነት ድርድር እንዳልተካሄደ ሲሆን አያይዞ ለድርድሩ በደመቀ መኮንን የሚመራ አካል ሥራውን እንደጀመረ ተናግሯል።የአብይ ማምታታት የተለመደ ስለሆነ ለሕዝቡ አዲስ አይሆንበትም ፣ ለእኛም እንዲሁ!የድርድሩ መቋጫ ወያኔ በሚፈልገው መልኩ እንደሚሆን ግን ሂደቱን የተከታተለና የኦሕዴድ ኦነግን አቋም ለሚያውቅና ለተረዳ ሰው እንግዳ አይሆንበትም ፤ውዥንብርም አይፈጥርበትም።በሥልጣን ክፍያና ወልቃይትና ራያን አሳልፎ በመስጠት አለያም በነጻ ተገንጥለው እንዲኖሩ በመፍቀድ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ቀድሞ ይረዳዋል።ይህ ግን አገሪቱን ለበለጠ ውድመት አማራውን ለማያባራ ጦርነት ይዳርገዋል እንጂ በሰላም የሚኖር የጎሳ ክልል አይኖርም።

ሌላው ስለሽግግር መንግሥቱ የተነሳውን ጥያቄ በሚመለከት አሁንም እኔ አሻግራለሁ በሚለው አቋምዎ ላይ ነዎት ወይ ?ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ የምን ሽግግር ነው?ሽግግሩን እኮ ሕዝቡ በምርጫ ካርድ አሶግዶታል።ለሚመጡት አምስትና አስርታት ዓመታት ቋሚ መንግሥቱን መስርቷል ሲል ከሥልጣን ሊንቀሳቀስ እንደማይችል አድርጎ ተናግሯል።አብይ አህመድ የካደው ነገር ቢኖር የገቡትን ቃል ለመፈጸም ያልቻሉ መንግሥታት በሕዝብ ተቃውሞ ከሥልጣን መባረር እንደሚችሉ ነው። ወያኔ በሕዝብ ተቃውሞ እንደተባረረና በክፍተቱ የሱ ድርጅት ኦሕዴድ ሥልጣኑን እንደተቆጣጠረ ረስቶታል።ነገም የእሱ እጣ እንደሚሆን ሊያውቀው በተገባ ነበር።በእሱና በተከታዮቹ እምነት ብልጽግና ቢወገድና የጎሳ ሥርዓቱ ቢፈርስ ኢትዮጵያ እንደማትኖር ነው።ይህ በቀድሞዎቹም መሪዎች ሲለፈፍ የኖረ መሆኑንና ፣ሲወድቁ ኢትዮጵያ አብራቸው እንዳልወደቀች ቢያስቡት መልካም ነው።

በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የኦሮሚያ ሕዝብ መዝሙር የማዘመርና የኦነግን ባንዲራ የማንጠልጠሉ ግዳጅ ፣የተረኝነቱ ማንአለብኝነት ያስነሳውን ሕዝባዊ ተቃውሞ በተመለከተ የሰጠው አደገኛ አስተያዬት የአብይን ክፋትና መሰሪነት ያሳዬ ነበር።የሌሎች አገሮች ማለትም የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣የጣልያን ---ወዘተ ትምህርት ቤቶች ያገራቸው መዝሙር በሚዘመርባት አዲስ አበባ እንዴት

የኦሮሞ ሕዝብ መዝሙር አይዘመርም ይባላል?ይህ ግልጽ ጸረ ኦሮሞ የሆነ አቋም ነው፤በዚህ መልኩ አገር በአንድነት ሊቆም አይችልም በማለት ኦሮሞን መንካት፣ተረኝነቱን መቃወም ኢትዮጵያን እንድናፈርሳት መገፋፋት ነው የሚል እድምታ ያለው ንግግሩን በንዴት አሰምቷል።እውነቱ ግን የውጭ አገር ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ያገራችንን መዝሙር ዘምሩ ብለው ያስገደዱበትና ያዘመሩበት አንድም ማስረጃ አለመኖሩ ነው።

ይህንን በሚልበት የፓርላማ አዳራሽ ውስጥ የአህዴድ ተወካይ የሆነችው ወ/ሮ ጫልቱ ንግግሯን በኦሮሙኛ ስትጀምር አብዛኛው ተሰብሳቢ ግራ ገብቶትና ምን እንደምትል ለመስማት የትርጉም መሣሪያውን በጆሮው ላይ ለማድረግ የፈጠረው ጫጫታ በራሱ ኦሮምኛ ብሔራዊ ቋንቋ ሊሆን እንደማይችል ማሳያ ነው።ከሌሎቹ ክልል የመጡት በሙሉ በአማርኛ መናገራቸው አማራ አላደረጋቸውም።ኢትዮጵያን የሚያድናት የነዚህ አይነቶቹ መኖር ነው።ኢትዮጵያን የሚበትነው የብዙሃኑን ቋንቋ  አማርኛ ጠል የሆነው እንጂ ሌላው አይደለም።ኦሮሚኛም ሆነ ሌላው በዬክልሉ የመነገር መብቱ ሊከበርለት ይገባል፤ክልል ዘለል የሆነውም አማርኛ በሁሉም ቦታ መነገሩ አማራው ማህበረሰብ የጣለው ጫና ሳይሆን በሕዝብ መስተጋብር ምክንያት የተፈጠረ መልካም ዕድል ነው።

ሕዝቡ በተለያዩ ቋንቋዎች ይዘምሩ ቢባል እንኳን በአማርኛ የሚዘመረው የሕዝብ መዝሙር በዬቋንቋዎቹ በትክክል ተተርጉሞ አማርኛ የማያውቁት በክልላቸው ይዘምሩት ቢባል የተሻለ ይሆን ነበር።መልእክቱ አንድ እስከሆነ ድረስ ችግር አይፈጥርም።ችግሩ ሌላውን ጠላት አድርጎ እንደባቢሎን ግንበኛ በዬቋንቋው ይንጫጫ ማለቱ ነው።ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን የጋራ አገር አያደርጋትም።ሕዝቡንም በአንድ ኢትዮጵያዊ መንፈስ አያሰልፈውም።ሕዝቡ እኮ ለውጥ ብሎ ሲነሳ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ይቀዬርልኝ፣ክ/ሃገር በክልል ይለወጥልኝ፣ኢትዮጵያዊነቴ  በጎሳ ማንነቴ ይቀዬር፣ ከሁሉም ጋር ፣የትም ሄጄ የምግባባበት የጋራ ቋንቋዬ አማርኛ ተወግዶ በሰፈር ቋንቋዬ ብቻ እዬተናገርኩ የሰፈሬ እስረኛ ሆኜ ልኑር አላለም።እኩልነት፣ፍትሕና የዜግነት መብቴ ይከበርልኝ ነው ያለው።በውጭ አገር ቋንቋ መናገሩና በውጭ አገር ፊደል መጻፉ ሰብአዊ ክብሩን አያረጋግጥለትም።ጭራሽ ለባርነቱ ማህተም ይሆናል።በቅኝ ግዛት በወደቁ አገሮች ላይ የደረሰው የማንነት ስብራት የዚያ ማሳያ ነው። የሚያሳፍር እንጂ የሚያኮራ አይደለም።

በአጠቃላይ የፓርላማው ውሎ ሲታይ እንደተለመደው ጊዜ አጭበርብሬ አልፍበታለሁ ያለውን በሩን የዘጋበት ይመስላል።አብይ አህመድ የተጋለጠበት እንጂ  የተሳካለት ውሎ አልነበረም።

ሌላው ትዝብታችን የወልቃይትና ራያ ጉዳይ የአገር ውስጥ ጉዳይ ስለሆነ የውጭ መንግሥታትም ሆኑ ድርጅቶች ጣልቃ ሊገቡበት አይገባም።ችግሩ ወያኔ አመጣሽ በመሆኑ፣ውይይቱ ችግር ፈጣሪውን ያላካተተ  ከትግራይ፤ከአማራውና ከአፋሩ  በተውጣጡ ያገር ሽማግሌዎች፣የሃይማኖት መሪዎችና ምሑራን  መካከል ቢሆን ዘለቄታ ይኖረዋል።

የአባይ ግድብን በሚመስል መልኩ የሌላ አገር ሰዎችና መንግሥታት ጣልቃ እንዲገቡበት ማድረግ የበታችነትን የሚያሳይና ለውጭ መንግሥታት ፍላጎት ማጎብደድን ያመለክታል።የአባይ ግድብ የተለያዩ ተፋሰስ አገራትን  በተለይም ኢትዮጵያን፣ሱዳንንና ግብጽን  ስለሚመለከት የሚመለከታቸው አገሮች ከዚያም ባለፈ የአፍሪካ ህብረት በታዛቢነት የሚሳተፍበት ውይይት ማድረጉ የተሻለ ይሆናል።በምንም መልኩ ምዕራባውያንና በጉዳዩ የማያገባቸው መንግሥታት ጣልቃ እንዲገቡ ማድረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።ትርፉ የፖለቲካ መጫወቻ መሆን ነው።

የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን የኢትዮጵያን የአዬር ክልል ጥሶ ከጅቡቲ መቀሌ መግባቱ ተሰምቷል። የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ቢሮ ስለጉዳዩ የሰጠው ማብራሪያ ባይኖርም እውነት ከሆነ አሜሪካ

በሌሎቹ አገሮች ገብታ የመበታተኗን ሴራ በአገራችን ለመድገም የሚያረጋግጥ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያሉበት ድርጊቱን እንዲቃወሙና እንዲያወግዙ ለዳግም አድዋ እንዲዘጋጁ ጥሪ እናደርጋለን። የመሬትና የአፄር ክልሏን ማስከበር ያልቻለ መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ለበለጠ አደጋ ሳይዳርገን ማሶገድ ይኖርብናል።በምትኩ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የምንለውም ከዚህ አይነቱ መደፈር እንዲከላከልለን ነው።

መካድ የሌለበት መንግሥት ተብዬው ቡድን መድከም ብቻ ሳይሆን በመፈራረስ ላይ ነው።ለዚያም ማሳያው በያቅጣጫው የሚታዬው ሥርዓተአልበኝነትና ሽብር ነው። በሁሉም አካባቢ የሕዝብ ጩኸትና እሮሮ በዝቷል፣ዝርፊያና ሙስና ተስፋፍቷል።ችግርና ድህነቱ ፣ሰላም እጦቱ፣ጎሰኝነቱ የአገር አንድነቱን ቀጭን ገመድ ሊበጥሰው የተቃረበ ይመስላል።በዬከባቢው የጦርነቱና የግጭቱ ምህዳር እዬሰፋ መምጣቱን ታዝበናል።በወያኔ በኩል ትንኮሳውና ወረራው እንደቀጠለ ሲሆን በጋምቤላ ውስጥ የኦነግ፣ የጉሙዝ፣የቅማንትና የጋምቤላ ነጻ አውጭ ግንባር ነኝ የሚለው ድርጅት የጥምር ሃይል የጋምቤላን ከተማ ከቦ በመያዝ የክልሉን አመራር አሶግዶ ለመቆጣጠር ጫፍ ላይ የደረሰ ሙከራ አድርጓል።በዚህ ሙከራ ብዙ ንጹሓን ዜጎች ህይወታቸው ማለፉ ሲታወቅ የአሸባሪው ቡድንም አባላት መገደላቸውና መሸሻቸው በክልሉ ነዋሪዎች በኩል የተሰጠው መረጃ ያመለክታል።የከተማዋ ነዋሪ ላለፉት ሦስት ቀናት ከቤቱ መውጣት እንዳልቻለ፣የአገልግሎት ተቋማት ሆስፒታል፣ባንክ ቤቶችና ሱቆች መዘጋታቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።በጦርነቱ የተሳተፉት የኑዌር ተወላጆች የሆኑ የታጠቁ ስደተኞች መሆናቸውንም የገለጹ የከተማዋ ነዋሪ አልጠፉም።ይህ የሚያሳዬው ከ400ሽህ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት የተሰጣቸው የደቡብ ሱዳን ተወላጆች ይሆናል ተብሎ የሚፈራውን የከባቢውን አደጋ የሚያረጋግጥ ሆኗል።ያም አደጋ ጋምቤላን ቆርሶ የደቡብ ሱዳን አካል የማድረጉ ፍላጎት ነው። ሁኔታው አስከፊ በመሆኑም በራብ የሚሞተው ቁጥሩ እንደጨመረ ተገልጿል።እንኳንስ ዘንቦብሽ እንደውም እርጥብ ነሽ ሆነና የነበረው ችግር ሳይቀረፍ ሌላ ችግር ሲጨመርበት ከባቢው ምን እንደሚመስል ለመገመት አያዳግትም። በጋምቤላ የተከሰተው የሰሞኑ ጥቃት ብዙ ንፁሃን ዜጎችን ህይወት የቀሰፈ ሲሆን በቁጥጥር ሥር የዋሉ ያልታጠቁ ሰዎች በታጠቁ ሃይሎች የፍጥኝ ታስረው በአደባባይ በጥይት ተደብድበው መገደላቸው የሕግና ሥርዓት አልባነትን ያሳያል።የክልሉ የፖሊስና ልዩሃይል አባላት ቤት ለቤት እዬዞሩ ንጹሃንን ከቤታቸው በር ላይ በጥይት መጨፍጨፋቸውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተቋም በማስረጃ ይፋ አድርጓል። በሌላውም ከባቢ እንዲሁ የሚሞተውና የሚፈናቀለው ቁጥሩ ቀላል አይደለም።ማንነታቸው ባልታወቁ ታጣቂዎች በአይሱዚ ተጭነው ይሄዱ የነበሩ በብዛት ወጣቶች በጥይት ተደብድበው መሞታቸውን የሚያሳይ የቪዲዮ ማስረጃ ተሰራጭቶ ለማዬት ችለናል።

አብይ አህመድና ሽመልስ አብዲሳ ሌሎቹም የብልጽግና መሪዎች በተገኙበት የነቀምት ስብሰባ ዝግጅት ላይ ቦምብ ተጥሎ የብልጽግና ተወካይ የሆነው የወረዳው አስተዳዳሪ፣የፖሊስ ኮሚሽኑና ሌላ ባለሥልጣን መሞታቸው የወጣ ዜና ያረጋግጣል።እነአብይ gne በቦታው ስላልደረሱ ካደጋው ሊድኑ ችለዋል ተብሏል።ዝርዝሩ እያደር ይወጣል የሚል ግምት አለን።ወጣም ወረደ የአብይ አህመድና የጥቂት ሰዎች መወገድ ለውጥ ያመጣል ማለት አይደለም።ለስር ነቀል ለውጥ፣ጸረ ጎሳ የሆነ አገር ወዳድ የተደራጀ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መካሄድ አለበት።ብልጽግና ሳይወገድ በወንበር ለውጥ አብዲሳ በጋዲሳ፣ ከበደ በታደሰ፣አብርሃ በበርሄ፣ቢኪኖ በካሚኖ፣አህመድ በሙሃመድ---ወዘተ ቢለዋወጥ ለውጥ ማለት አይደለም። ያለፈው ይበቃል!!

በብልጽግና ውስጥ የተፈጠረው ውዝግብ አንዱ አሳዳጅ ሌላው ተሳዳጅ ከሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ፣ በተለያዩ የሥልጣን እርከኖች ላለፉት 31 ዓመታት የሥርዓቱ ቁንጮ ሆኖ የዘለቀውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ

በአብይ አህመድ ላይ ትችት ያነሳው የብአዴኑ ገዱ አንዳርጋቸው በአውሮፓ ምናልባትም በስዊድን ወይም በኖርወይ ጥገኝነት እንደጠዬቀ የሚያጋልጥ ዜና ተሰምቷል።ይህ በአንድ የዜና ስርጭት የተሰማ ወሬ በሌሎቹ ባይደገምም የገዱን ሁኔታ የተከታተለ ይህንን ከማድረግ እንደማይመለስ ይጠረጥራል። እኛም እንጠረጥራለን።ገዱ የመጀመሪያ ሳይሆን ባገኙት አጋጣሚ በውጭ አገር ለመኖር የወሰኑ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ወኪሎች ብዙ ናቸው።አንድ መንግሥት ሊወድቅ ሲቃረብ በውስጡ ትርምስ ሲፈጠር የማይቀር ድርጊት ስለሆነም ሊገርመን አይገባም።ከሕዝብ ጋር የወገነ፣ለሕዝቡ የቆመ መንግሥትን ያገለገለ ባለሥልጣን ኮርቶና ተከብሮ በአገሩ ይኖራል፣ለዚያ ያልታደለው የከንቱ ሥርዓት አገልጋይ የሆነ ሆድ አደር ደግሞ ከቻለ ይፈረጥጣል አለያም በድል ማግሥት በሚቋቋመው በህዝባዊው የፍትሕ ተቋም ፍርዱን ያገኛል።ከአህያ ቆዳ የተሰራ ከበሮ ጅብ ሲጮህ ይቀደዳል እንደሚባለው ጸረ ሕዝብ የሆነ ስብስብም ሕዝቡ ሲነሳ ብትንትኑ መውጣቱ አይቀሬ ነው።

የአብይ መንግሥት የሕዝቡን ትኩረትና ተቃውሞ ለመቀልበስ የማይገለብጠው ድንጋይ ፣ የማይጎነጉነው ሴራ አይኖርም።ሆኖም ግን የዓላማ ጽናት ያለው፣መነሻና መድረሻውን የሚያውቅ፣ ሕዝብ በጥቃቅን ማታለያዎችና ጉዳቶች ፍርሃት ትግሉን ማቀዝቀዝ አይኖርበትም፣ወደ ትግል ሲገቡ ሊገጥሙ የሚችሉትን ውጣ ውረዶች ለመቀበል የአካልና የመንፈስ ዝግጅት ማድረግ ተገቢ ነው።ውጣ ውረዱን ችሎ በትግሉ ከገፋበት ግዙፍ አገራዊ ችግሮችንና ጠላቶቹን ለማሸነፍ የሚያግደው ሃይል አይኖርም፣ይህ አገር አጥፊ የጎሰኞች ስርዓት እስኪወገድና የአገርን አንድነት፣ልዑላዊነትና ዳር ድንበር፣ የሕዝብ እኩልነት ፣ መብትና ክብር የሚችል ሥርዓት እስኪዘረጋ ድረስ ትግሉ መፋፋም አለበት። ጀግኖች የማይጨርሱትን አይጀምሩትምና!

ለአገር ልዑላዊነትና አንድነት ሁሉም ዘብ ይቁም!

የአማራው ፋኖ ትግል የሁሉም ሕዝብ ትግል ነው!!ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማስከበር ነው!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!